# የመጨረሻው ሰይጣን
# ክፍል ስድስት

ከበልጅግ አሊ

- እንደምን አደሩ ደህና አደሩ።አልጋውስ ተስማማዎት?
- በጣም እንጂ ። ማለፊያ አልጋ ነው። የወደቁበትን ሳላውቀው ነጋ።
- ይህች ልጅ መቼም ምንም እረፍት አልሰጠችኋትም። አሁን ደግሞ የት ሄደች?
- ዳቦ ገዝቼልሽ ልምጣ ብላ ወጣች። ቶሎ ነው የምትማረው።አንዳንዱን ቃላት አታውቅም እንጂ ምንም አትል ቶሎ ይገባታል። እንቡሼ ገላን ነበር ያስተማርኩኋት።ድሮ ሕፃን ሆነን የምንጫወተውን።

እንቡሼ ጋላ
ያብሽ ገለባ
ሜዳ ነው ብዬ
ገደል ልገባ
ገደል ገብቼ
ልወጣ ስል
ጅቡ መጣብኝ
ከቂጤ ስር።

እንል ነበር።ከዛም

እቴ እሜቴ የሎሚ ሽታ
ያ ሰውዬ ምን አለሽ ማታ።

ምንም ምንም ምንም አላለኝ
ትዳሩን ፈቶ ልውሰድሽ አለኝ።

አይወስድሽም ትዳሩን ፈቶ
ምሎላታል ጋሻ ጦር ነክቶ።

ከቤቴ ባላይ ቁራ ሰፍሮ
የለችም ቢሉት ሄደ በሮ።
እኔን ያብረኝ ያክንፈኝ
የዝሆን አሞት ያስጠጣኝ።

የዝሆን አሞት መራራ ነው
የጀግና ልቡ ተራራ ነው።

ተራራ ወጥቶ ሲመለስ
አህያ ሞቶ ጅብ ሲያለቅስ
ቀበሮ ቆሞ ሲቀድስ
እባብ አንገቱን ሲነቀስ።

እሂን ነው ያስተማርኩዋት።ነገ ደግሞ ሌላውን። አየህ ልጆቹ መማር ይፈልጋሉ ወላጆቹ ካስተማራችሁኋቸው ድግሞ ይገባቸኋል።

አየህ ያ ጨካኝ ጭከናን ከአባቱ ነው የተማረው ማለት ይቻላል።ወረሰው ማለት እንኳ ባንችልም አስተዳደግ ወሳኝነትም አለው። የሽማግሌዎቹን ምክር እንደገና አሰብኩት ግን እርቅ ከልብ ካልሆን እኮ አይሰራም። እርቅ የሚረጋው ደግሞ በዳይ መበደሉን ከልቡ ሲቀበለውና ተበዳይ ደግሞ ከልብ ሆኖ ሲያገኘው ብቻ ነው።በዳዩ የበደለውን እንደበደል ሳይቆጥረውና ምክንያት እየፈለገ ተበዳይ ሆኖ ለመቅረብ ጥረት የሚያደርግ ከሆነ እርቁ የውሸት ነው የሚሆነው።የሚች ዘመዶች ጊዜ ነው የጠበቁት። ልጆቻችው እስከሚያድጉላቸው የሚከላከልላቸው እስከሚያገኙ ድረስ በሰቆቃ እየኖሩ ነው ጊዜያቸውን ያሳለፉት ።ገዳይም ቢሆን የሰነበተው የከፈለው ካሳ እየቆጨው በየመንገዱ ጥርሱን እየነከሰ ሲያስፈራራቸው ነው።ሁሉም ነገር እየተለወጠ የመጣው ልጆቻቸው ሲደርሱላቸው እሱም እያደረ እያረጀ ሲመጣ ነው ።

እስቲ ተመልከተው። ልጄን ገለው እኛን የፀረ አብዮተኛ ቤተሰብ እያሉ ከቀበሌም ከሁሉም አግደው ለአስራ ሰባት አመት ሲያሰቃዮን ከርመው አገሪቱዋን ጥለው ጠፉ ። አሁንም ቢሆን ያጠፉት ሕይወት ሳይቆጫቸው እንዲያውም ትክክል እንደሆነና እነርሱ ተበደይ ሆነው ሊቀርቡ ይፈልጋሉ። የአሁኑም መንግስት ቀይሽብርን እየተጠቀመ ሲጠነክሩበት በሱ ያስፈራራና ለሱ እንዲሰሩ ያደርጋቸዋል። እንግዲህ የኛን የአሮጊቶቹንና ሽማግሌዎቹን በደል አለጡዋሪ መቅረት ማን ነው የሚየይልን። ግማሾችም አሁንም ቢሆን የዘረፉትን ገንዘብ እንደያዙ በየውጭ አገሩ ሲዝናኑና የተቃዋሚ ድርጅቶችን በውስጥ እየረዱ በዛውም ደግሞ ተቃዋሚዎቹ ለእነርሱ እንዲሰሩ እያደረጉ ተቀምጠዋል።

እኔ የልጄን ገዳይ ባገኘው የምጠይቀው ለምን ልጄን እንገደለው ነው። ምክንያቱን ማወቅ በጣም ነው የምፈልገው። ይቅርታም ባደርግለት እኔ እናቱ ነኝ ይቅር የምለው። እኔ ነኝ አምጫ የወለድኩት። እኔ ነኝ ዘጠኝ ወር የተሸከምኩት። የልጄን ገዳይ ይቀር ብልም እኔ ነኝ።የልጄን አፅሜ እኔ ነኝ የምለቅመው እንጂ የልጄ ጠላት ለህዝብ ድጋፍ ማግኛ ሊያደርገው አይገባም። እርቅም ቢደረግ እኛ ያለንበት ነው። እኛ ካለ ጡረታ ከአለ ልጅ የቀረነው ሳንገባበት ሌሎች በእኛ ስም እርቅ አደረግን ቢሉን አንስማማም ። ሀውልት እንኳን ላልተሰራላቸው ልጆቻችን ከኛ በላይ ማን ሊያስባቸው ነው ። ልጄ እኔ አሮጊት ነኝ ።የመጀመሪያ ልጄን አጥቼአለሁ። እሬሳውን እቤቴ በራፍ ላይ ተጥሎ አግንቻለሁ ። ለኔ ይቅር ለማለት ይከብደኛል።ላንተም አካልህ በግርፍ ለጎደለው እንደኔው ይመሰለኛል። ስለዚህ ሌሎች በእኛ ስም ቢታረቁ እሺ እንደማንል ስለሚታወቅ በእኛ ስም ሌሎች ቢያደርጉት ተገቢ ሆኖ አናገኘውም።

ከሁሉ የሚያናድደኝ ቢኖር እሱ ያረጀ ታሪክ ነው ተውት የሚሉት ናቸው።እንዴት ነው የምንተወው ብዬ ብጠይቅም መልስ የለም ።ብቻ እሱን አታንሱት ይሉናል። እኛ ብንተወውም እነርሱ ግን አይተውትም በሌላ ሌላ ሲወጉን በቁስላችን እንጨት እየሰደዱበት ነው። ብዙዎቻችን አርጅተናል። ሕይወታችንን በሙሉ በሃዘን አሳልፈናል። ከአሁን በኋላ ለኛ ብዙ የሚለወጥ ነገር ላይኖር ይችላል።ባለፈው ጊዜ አንድ ሶስት ልጅ የሞተባቸቸው ሰውዬ እቤተክርስቲያን አግኝቼ ነበር። ገና እንደ አዲስ ለቅሶ እንባቸው እየወረደ ያሉኝ ነገር እስካሁን ያስለቅሰኛል። በጨዋታ በጨዋታ ተነስቶ ልጆቹ ቢኖሩ

ኖሮ ውጭ አገር እንደ ሌሎቹ ሄደው ይረዱኝ ነበር። ቤቴንም ያድሱልኝ ነበር።የጎረቤቱ ቤት ሁሉ ታድሶ የኔ ቤት ግን እንደፈረሰ ቀረ አሉኝ። ታዲያ እኝህ ሽማግሌ ማነው የሚያስታውሳቸው። ወይስ ያረጀ ታሪክ ነውና እርሱት ነው የሚባሉት። እሳቸው እኮ እስካሁን ድረስ እየተጎዱ ናቸው። ለአንዳንዶቻችን እኮ ገና አዲስ ነው።ከሁሉም የሚናድደኝ ከልጄ ከሚቹ ጓደኞች ይህንን ስሰማው ነው።

እዚህ ላይ ነው ታዲያ ለሚች ዘመዶች ጊዜቸውን ጠብቀው ለመበቀል የሄዱት።እኛን ግን ማንም የሚበቀልልን የለም ። የልጆቻችን ጠላት የነበረው ወያኔ የልጆቻችንን ደም እንደገና ማፍሰስ ይፈልግ እንደሆን እንጂ ይበቀልልናል ብለን አናስብም።በቀልም አደለም የምንፈልገው በኢሰፓ ካድሬዎች የሚቾቹን ስም ለማጥፋት የሚደረገው ጥረት መቆም አለበት። በጣም የተጎዱ ቤተሰቦች የሚረዱበት መንገድ ሊፈለግ ይገባል ነው የምለው። ሽማግሌው ቤታቸው እራሳቸው ላይ ፈርሶ እስከሚያለቅ ድረስ ተጠበቀ። ብዙዎቹ ሞተው አለቁ የቀሩትን እንኳን መርዳት ቢቻል እንደተካሱ እንቆጥር ነበር። ግን ያ ሳይደረግ እርቅ ቢባል ምንም ፋይዳ የለውም። የደርግ አባላት፣ እራሱም መንግስቱም ጭምር ብዙ ገንዘብ ይዘው እንደጠፉ ይታወቃል። ታዲያ አለም ላይ ፍትህ ካለ ለነዚህ ሽማግሌዎች ትንሽ እርዳታ ከሱ ላይ ቢሰጡ እንኳን እንታረቅ ቢባል መልካም ነበር። ግን በዛ ገንዘብ መልሰው እኛን ሊወጉን ሲነርሱ የምን እርቅ ነው ሊሆን የሚችለው። ልጄ ተወኝ እባክህ።

- እንዴት ነበር ወያኔ የገባ ግዜ አፅም ለቀማው?

- እሱን ጓደኛህን ጠይቀው። እሱ የዚያን ግዜ በጣም ነበር የተራወጠው። እሷን የልጅነት ፍቅሩንና ጓዶቹን ያገኘ መስሎት ትልቅ ጥረት ነው ያደረገው።እኔ ግን አንድ ነገር ተገንዝቤያለሁ። ኢሕአፓ የሕዝብ ድጋፍ እንዳለው፤ ባይኖረው ወያኔ ያንን ለመጠቀም ባልፈለገ ነበር።ዛሬ በየቦታው የሚያናፉት የደርግ ካድሬዎች ወያኔ ቢወርድ እንኳን ወደ ፍርድ መቅረብ እንዳለባቸው ግልፅ ሊሆን ይገባል።እርቅም ከተባለ ያጠፉትን ሁሉ ማመን አለባቸው። አለበለዛ ግን ቂሙ ከዘር እዘር እንደሚተላለፍ እንዳትጠረጥረኝ።ያን ግዜ የነበረው ሁኔታ የተዋከበ ስለነበረና አላማው ለወያኔ የድጋፍ ማግኛ ስለነበረ ማንም ለሞቱት ቦታ የሰጠ አልነበረም። ህዝቡም ወያኔን ላለማስደሰት ብሎ በነዚህ አረመኔዎች ላይ ፍርድ ለመስጠት ተቆጠበ።
- በሉ እስቲ ዛሬ የኔንና የጓደኛዬን ደብዳቤ ላንብብት።
- ይሻላል ልጄ ።
- መጀመርያ የኔን ቀጥዬ ደግሞ የሱን ።

ውድ ጓደኛዬ

መኖር ከማንም ጋር ይኖራል መለያየትም እንደዚሁ።በአእምሮ ጽላት ውስጥ በማይፋቅ ቀለም የሚፃፍ ጓደኛ ማግኘት ግን ከሁሉ የበለጠ የሕይወት ብሩሐ ተስፋ ነው።እንዳንተ አይነት ጓደኛ መግኘት እንደሚከብድ ባውቀውም አሁን በመካከላችን ያለውን ሁኔታ ሳልመለከት በድሮው ፍቅራችን አንድ ጥያቄ ለመጠየቅ እፈልጋለሁ።

እስከዛሬ ለፃፍኩልህ ደብዳቤዎች መልስ እንዳልፃፍክልኝ ባውቀውም ዛሬ እናትህ ስለመጡ ቀን በቀን ስላንተ ማሰቤ አልቀረም።ስለዚህ ነው አንተን የማልረሳህን ጓደኛዬን እንዲህ በቀላሉ ላጣህ እንደማልፈልግ ልታውቀው ይገባል የምልህ። ያጠፋሁት ካለ እንደ ድሮው ጠባያችን ሂስ ልትሰጠኝ ሲገባ ምንም ሳትነገረኝ ግኑኝነታችንን ለብዙ ግዜ ተቆርጦ ገና ከመጀመሩ መሸሽህ በጣም ነው ያሳሰበኝና ያሳዘነኝ። ግን ቢሆንም አሁን ደግሜ ትዝታዬን አካፍልሃለሁ።ሁልቀን የማስበው አንድ ነገር አለ ይኸውም ከአንተ ጋር ለመሆኑ ለመጨረሻ የተያየነው የት ነው? ግዜው በመርዘሙ ነው መሰለኝ አሁን ግልፅ የሆነ ሃሳብ የለኝም።

ወድ ጓደኛዬ

መጨረሻ የት እንደተያየን ለማስታወስ ስፈልግ ትላንት ይመስለኛል። መርካቶ ይሁን ፒያሳ ወይስ ሰፈራችን ለማስታወስ ያዳግተኛል። ትንሽ ትዝ የሚለኝ በተቀጠቀጠ ሰውነቴ ፣ ሊያጣራ በማይችለው ዐይኔ ፣ ከርቸሌ ግቢ ውስጥ ውድ ጎደኛዬ ለመጨረሻ ግዜ አይተኸኝ እንደተሰወርክ እንደህልም ይታወሰኛል።አሁን ልጠይቅህ የምፈልገው ፡ ለመሆኑ በመጨረሻ የት ነበር የተያየነው? አትፍረድብኝ አንተን ለመርሳት ብዬ አደለም። በህይወት ዘመኔ አንተን የረሳሁበት ግዜ የለም።የስቃዩ ብዛት ነው መሰለኝ ትዝታዎቼ በሙሉ ተኝቼ እንዳሳለፍኩት ጊዜ እንደ ሕልም ነው የሚታወሰኝ።በተለይ የዚህ አገር ብርድ በጠነከረ ግዜ ድሮ የተገረፈ እግሬን ሲጠዘጥዘኝ አዕምሮዬን እየሰለበ ያለፈውን ግዜ እንድረሳው ይሚገተኛል።ህይወቴ የሚጥም ያልተጨረሰ መፀሃፍ ይመስል የት ላይ እንዳቆምኩት ለማስታወሰ ስጥር እኖራለሁ።ልታውቀው ከፈለግህ ይህ ነው የዘንድሮ ኑሮዬ ፣ አይረባም፣ አይጥምም፣ እንከፍ ነው፣ አላማ የለውም ፣ ለዛሬ ነው የምኖረው፣ ለነገና ለብሩሕ የወደፊት ቀን መኖር ካቆምኩ ሰንብቻለሁ።

ዛሬ ምን ብዬ እንደምጀምር ግራ ቢገባኝም የኔን ቀለል የሚየደርገው አንተ የተከታተልከው የሕይወት ታሪክ ስላለኝ ነዉ። በሄድኩበት ቦታ ሁሉ በሃሳብህ ትከታተለኛነህ። አዋሳ ብሄድ ኢሊባቡር ብመደብ ወይም ከሀገር ብወጣ አብረህኝ ነው ያለኸው።እኔ ከራሴ ጋር ስሚገት አንተ አጠገቤ እንዳለህ ላንተ የምነግርህ እየመሰለኝ ብዙ ጊዜ በሃሳቤ አካፍልሃለሁ። ጥቃቅኑን ነገር አታውቀው ይሆናል።ብዙ የምንግርህ ነገር የለኝም።በአውሮፓ አልባሌ ኑሮ እኖራለሁ። ይኼኛው ኑሮዬ ብዙም ስለማይጥመኝ ወደ በኋላ እመለስበታለሁ።

ከእስር ቤት ተፈትቼ የቂም ስቅሌን ቢያሳዩኝ፡ ከነርሱ የተገላገልኩ መሰሎኝ እርሻ ተምሬ ገጠር ገባሁ።ኢሊባቡር ነበር የሄድኩት። እነርሱ የሌሉ መስሎኝ።ምን የሌሉበት ቦታ አለና፣በሰው የተመሰሉ የሰይጣን ቁራጮች፣በደም የተጨማለቀ እጃቸው በህልማቸወ የሚያስጮሀቸው፣አላጋጠመህም ወዳጄ በሄድክበት በአለህበት።አላስቀምጥ ቢሉኝ ፡ እነዚህ እርጉሞች ብዙም አልጠበቅኋቸውም ጥዬ ወደ ዋናዎቹ ወደ ሶቬት ሕብረት ሄድኩ።በትህሳስ ወደ ጀርመን ሄጄ የሰላም አየር እተነፍሳሉ ስል በመስከረም መወጣት ከልክለው እዛው ሶስት አመት አገቱኝ፡፣ እዛ ነው ተምሬ በእርሻ ትምህርት የተመረቅሁ፡፣ታሪኩን ፅፌ ለማስቀመጥ ሳስብ ብዙ ዘመን ሆነኝ። ነገ ዛሬ ስል እዚህ ደርሻለሁ።

ስለኔ ታሪክ ለማወቅ እንደምትጓጓ እማማ አጫውቱኝ። እኔም በጥያቄ ልባቸውን ባወልቀው ነው መሰል ፃፍለት ብለው ጨቀጨቁኝ ።እንደምታውቀው የአንተ እናት በጣም አስተዋይ ናቸው።ብዙ ነገር እንጫወታለን። ብዙ ከእሳቸው እማራለሁ።

የምናመሽው መቼም ስላንተ የማወቅ ፍላጉቴን ስላወቁ ነው መሰለኝ እሱን ሳነሳ እሳቸው ላለመንገር ሲሸሹ ነው ። ምክንያቱም ይገባኛል እኔና አንተ እንድንፃፃፍ ታላቅ ፍላጎት ነው ያላቸው። እሳቸው እንደሚሉት "ይህ የኔ ሃሳብ ነው እሱን ደግሞ ጠይቀው የእርሱ ይለይ ይሆናል“ ነው የሚሉኝ። እሳቸው ከአገኘሁ በኋላ ከብዙ ግዜ በኋላ ሰፈር የገባሁ መስሎ ነው የሚታየኝ። ብዙ ስለኔ ያለፈ ህይወት ማወቅ እንደምትፈልግ እማማ ነግረውኛል። እኔም ስላንተ ማወቅ እፈልጋለሁ። ስለዚህ የዚህን ደብዳቤ መልስ ሳገኝ በቀጥታ ስላለው ታሪኬ ደብዳቤ ለመፃፍ ቃል እገባልሃለሁ።ለአሁኑ ግን

ስለኛ የሚያሰብ በሰላም ይክረም።

ጓደኛህ

ውድ ጓደኛዬ

እናቴ እናንት ጋር ከመጣች ጀምሮ ስለአንተ ማሰቤ የታወቀ ነው ። አንተም ያህንን አላጣኸውም ። እሷ እንደምትለኝ ከሆነ በኔ ላይ ተስፋ አልቆረጥክም ። እኔስ በአንተ ላይ ተስፋ እቆርጣለሁ ብለህ ታስባለህ? ባለፈው ሳምንት እቤት ተቀምጬ ስልኩ ሲጠራ ወትሮዬን የምጠብቀው ምንም ነገር ስለሌለ ስልክ ማንሳት የማልወደውን ያህል ታላቅ መልክት ያለኝ ይመስል ተንደርድሬ ባነሳው ያገኘሁት እናቴን ነው።

ምን እንደእንደነገርካት አላውቅም። እናቴ በጠባሁት ጡት፣ እትብቱ በተቀበረበትና፣ በምወዳቸው ልጆቼ፣ስም እሺ እንድላት ከለመነችኝ በኋላ ለአንተ ደብዳቤ መልስ እንድሰጥ ጠየቀች።እኔም ብሆን ጥንትም ለአንተ ያለኝ ፍቅር ምንም ያልቀነሰም ስለነበረ ወዲያው ተስማማሁላት ።ቀድሞም የታሰበ ነውና ወዲያው ጀመርኩ።

የሰማዩን እርቀት፣የውቅያኖስን ጥልቀት፣የምድርን ስፋት፣ብዬ ጀመርኩ አልጣመኝም ቀደድኩት። እንደምን ከርመሃል ብዬ ጀመርኩ።እንደምን እንደከረምክ ሳውቀው ምን ያስፈልጋል ብዬ አሰብኩ። ቢሆንም እንዴት እንደከረምክ እኔ አሰብኩት እንጂ አንተ ስላልነገርከኝ ከአንተ መስማት ፈለግሁ ። ያንተን ደብዳቤ እንደገና ተመለከትኩት ።

„መኖር ከማንም ጋር ይኖራል መለያየትም እንደዚሁ ።በአዕምሮ ፅላት ውስጥ በማይፋቅ ቀለም የሚፃፍ ጓደኛ ማግኘት ግን ከምንም የላቀ የህይወት ብሩህ ተስፋ ነው።„ አልከኝ።

አሁን አደለም ያወቅሁት ከአንተ የበለጠ በኔ ልብ ውስጥ የተፃፈ ውድ ጓደኛ እንደሌለኝ ።ድሮም ቢሆን አንተም ሳትፅፈው ስላንተ ያለኝን አስተሳሰብ አንተም ትገምተዋለህ ። እኔም አውቀዋለሁ ።ያኔ በክፉው ዘመን የምገኝበትን ቦታ አጥተኸው አልነበረም እንደዚህ ሲቀጠቅጡህ ችለህ ደብቀህ ይዘህ ብቻህን የተወጣኸው ።

ያ ሁሉ ሲሆን የት ነበርክ አልከኝ። እኔማ ከአንተው ጋር ነበርኩ ።ምን ሆኖ ይሆን በሚለው አሳብ ነፍሴ ተሳቅላ በእሰሳ፣በነፃ እርምጃ፣ መግቢያ መውጫ አጥቼ ስንከራተት ነበርኩ።ወንድሜን እንዳላድንህ አቅሙን አጥቼ በማዴቦ እስኳድ፣ በነፃ እርምጃ፣ እንድመታ ተወስኖብኝ ከተማውን እየዞሩ ሲፈልጉኝ የአንተ መታሰር እያንገበገበኝ እየተንከራተትኩ ነበርኩ።ሌላ ምን እሆናለሁ ብለህ ። የማደርገው ባጣ ስለ አንተን ወሬ ፍለጋ ተደብቄ ሰፈር ሄድኩኝ።ያገኘሁት ግን አንተ የገባህበት ያልታወቀ መሆኑን ነው ። ቀኑ እየገፋ ሲመጣ ትኖራለህ የሚለው ተስፋ እየመነመነ መጣ ። አንድ ቀን ፤ ሁለት

ቀን ፤ ሶስት ቀን ፤ የት እንዳለህ ምንም ወሬ የለም ። በየእስርቤቱ መንከራተት ሆነ ። ሁሉንም እስርቤት ማዳረስ ከቁጥሩ ብዛት የተነሳ አልተቻለም። በኔ በኩል ግን አንተ ሚስጥር እንደማታወጣ ምንም ጥርጥር የለኝም።ቢሰቅሉህ ቢገርፉህ አጥንትህን ቢሰባበሩት ምንም እንደማያገኙ አውቅ ነበር ። አምስት ቀን ፤ ስድስት ቀን አለፈ። እዚህ ቦታ እሬሳ ወድቆአል ከተባለ መሮጥ ነው ። ለኔም ወደ ሰፈር መግባት አደጋኛ እየሆነ መጣ ።

አልችል ስል ቀስ ብዬ ስፈር ተመልሼ እመጣና እጠይቃለሁ ። ሰባት ቀን ስምንት ቀን ምንም ወሬ ጠፋ ። አንዳንዴ ሰፈር የምሄደው እንደው ድንኳን ተጥሎ እንደሆን ብዬ ነው። አካባቢው ሁሉ ፀጥ ካለ ደግሞ አዲስ ነገር እንደሌለ አስቤ እመለሳለሁ ። ከከተማው የሚመጣው ወሬ ሁሉ የሚስጠላ ሆነ ። በየቦታው እሬሳ ተጥሎአል የሚለው ወሬ እየበዛ መጣ ። በየጫካው በጅብ ተጀምሮ ያልተጨረሰ አስከሬን ማግኘት የቀኑ ወሬ ሆነ።

የት ነበርክ አልከኝ ? የት እሆናለሁ ብለህ ። ቀን ቀን የአንተን ሬሳ ፍለጋ ማታ ማታ ደግሞ ያንተን ወሬ ፍለጋ ። ዘጠኝ ቀን አስር ቀን አለፈ ። ጥዬ ወደ ሌላ አገር እንዳልሄድ ልቤ በአንተ አልጨክን አለ ።

አስራ አንድ ቀን አስር ሁለት ቀን አለፈ ምንም ወሬ ጠፋ ። ቀበሌ አምስተኛ ፓሊስ ጣቢያ ነው ይላል ። አምስተኛ ፖሊስ ጣቢያ ደግሞ አናውቅም ይላል ።እስኪ ማዕከላዊ ፈልጉ ይባላል ። ማዕከላዊ ሲኬድ ደግሞ ወደ ደርግ ፅህፈት ቤት እስኪ ፈልጉ ይባላል ። ሌላም ሌላም ይወራል።

አስራ ሶስት ቀን አስራት ቀን ተገኘ ተባለ ። ከርቸሌ ነው ያለው ግን መኖር አያበለው እንጂ አለ ተባለ ። ሰፈሩን እፎይታ ሞላው ። እኔም ለጊዜውም ቢሆን እፎይ አልኩ ። አሁን ሳስበው ስለአንተ ማሰብ ሌላውን ያለብኝን ችግር አረሳስቶ አለምን ለኔ አቁሙዋት ነበር ። መገኘትህን ሳውቅ ያለበኝ ችግር ሁሉ ከሩቅ ወደ ቅርብ መጣ ። ግን ቢሆንም ለመጨረሻም ቢሆን አንተን ማየት ፈለግሁ ። ነፃ እርምጃ ያሳድደኛል፣ አስሳ ይከተለኛል ፣እርሃብ ጥማቱ በዝቶብኛል። ለስደት የተመደበልኝ መጠለያ አደጋ እየበዛበት መጥቶአል ።

ባለፈው ደብዳቤህ ለመጨረሻ የት ነው የተያየነው ብለህ ጠይቀኸኝ ነበር ። ተደብቄ ከርቸሌ መጣሁ ። አንዲት አሮጊት ከኔ ቀድመው ተሰልፈው ስሰነበር የያዙትን እቃ እየረዳኋቸው ወደ ፊት ቀጠልን። ፓሊሱ ማን ጋር እንደምንገባ ሲጠይቅ እሳቸው መለሱ። እኔም አብሬአቸው ስለነበርኩ ከእሳቸው ጋራ ታስቤ ገባሁ ። ትንሽ እንደሄድኩ የሰፈር ሰው ተስብስቦ አየሁ ሁሉም አላወቁኝም ነበር ። ተጠጋሁ አንተ የለህም ሁሉም ይጠብቀሃል ከዛ በቃሬዛ ተሸክመውህ መጡ ።

እንባ አነቀኝ ጉልበቴ ከዳኝ ። አንድ የምወደውን ጓደኛዬን ወንድሜን እግርህን ተልትለው ያ የምመካበትን ትልቁን ቁመናህን ቀንሰው ቀናንሰው አሳንሰው ማየት ያስደነገጠኝን ያህል ቆራጥም አደረገኝ ።መፍራት አቆምኩ፣ነፃ እርምጃ፣ ማዴቦ ስስኳድ፣ አብዮት ጥበቃ፣ መፍራት አቆምኩ ። ለማን ፣ንጉሴን ፣ አርጋውን ፣ደስታን፣ ሙልጌታ ፣ ከሰተህ ፣ ሀይለማርያምንን ፣ ይግረምን ፣ ካሳን ፣ ጌታቸውን ፣ ትንሳኤን ፣ ለሎቹንም ጭምር እረሳኋቸው። ለኔ ህይወቴ የቆመችው የዛን ግዜ ነው ። አብረን አደገን፣ አብረን ኖረን አንድ ቀን እንኳ ሳንለያይ አሁን አንተ በቃሬዛ ሆነህ አንተን መርዳት አቅቶኝ መመልከት የመጨረሻ በቁም የሚትኩ መሆኔን አስረዳኝ ። አንተ በእኔ ቦታ ብትሆን ኖሮ ብዬ ሳስበው ምን የማትፈነቅለው ነገር አለ።አሁን ወስኛለሁ አንተ የተቀበልከውን

ስቃይ ሁሉ ቤተሰቦቼ አይቀበሉም ። ከዚህ እንደወጣሁ ሂጄ እጄን እሰጣለሁ ብዬ ወሰንኩ ።

ባለፈው ሳምንት አንተ እንደታሰርክ ለቤት መልክት ልኬ ስለነበር መልሱን ለመጠየቅ አባቴ ጋ ጠጋ ብል እሱም አላወቀኝም ነበር ። ቀስ ብዬ እኔ መሆኔን ነገርኩት ። ግዜ ሳያጠፋ አንድ ነገር አስረዳኝ ።

„ አንተ ከዛሬ ጀምሮ ለኛ የሞትክ ነህ ። ቅዳሜ በቀይ ሽብር እንደተመታህና እሩቅ ሰፈር ወድቀህ እንደተገኘህ ተደርጎ መርዶ እንቀመጣለን። የሚያረዱንም ሰዎችም ተዘጋሰጅተዋል። አንተም ከዚህ ጥፋ እንዳትገኝ ማምለጫ መንገድ ከሌለህ እኛ እናግዝሃለን ። ከሽማግሌው ጋር ተወያይተን ነው የወሰነው እናትህ አዘኑ እንደሚጎዳት እናውቃለን ። ቢሆንም ነገሩን ለማሳመን እናትህ አለመስማትዋን አምነንበታል ። የገደልንህ አንተን ለማዳን ስለሆነ ሞትህን በደስታ ተቀበለው ። እኛን ለማግኘት ብለህ የብዙዎቻችንን ህይወት አደጋ ላይ እንደማትጥል እተማመንብሃለው ። አንተም ደግሞ እራስህን ጠብቅ ። አካባቢህን ለመምሰል አትሞክር። አንዳንድ ጊዜ አካባቢ ሞኝ ነውና አካባቢን መምስል ሞኝነት ይሆናል ። ጊዜ ያልፋል እስከሚያልፍም ያለፋል። ምን አይነት ኑሮ የሞተ ሰው እንደሚኖር አላውቅምና ምንም ልመክርህ አልችልም። እግዚሃብሔር ከፈቀደ ወደ ፊት ትነግረኛለህ ። ችግር እንደሚገጥምህን አልጠራጠርም ። የሆነ ሆኖ እንደ ጓደኛህ ችግሩን ወደ ሌላ እንደማታስተላልፍ አምናለው ። ጓደኛህ በሀዘን ውስጥ ደስታን ለቤተሰቦቹ ሰጥቶሰቸዋል ። ልጃችሁ ልጃችንን እንዲ አደረገብን የሚላቸው አይኖርም ።አንተም እኛን ሽማግሌዎቹን በስተርጅና ቀባሪ አታሳጣንም ብዬ አምናለሁ ። ብዙ ምስጥር ታውቅ ይሆናል ልጄ ያንንም ያመንክበት ስለሆነ ጠብቀው ። በቆራጥነትህ በአላማህ ፅናት እንደምትከበር እንዳትጠራጠር ። በትንንሽ ሁኔታ አሳብህን ለመቀየር እንዳትሞክር።ምክንያቱም በጊዜያዊ ሁኔታ እንዳትደለል ወይም እንዳታመነታ እፈልጋለሁ ። ትንንሽ ድሎች መጨረሻ ላይ ሊቀየሩ ይችላሉ“።

„ልጄ የሞትክ ነህና አዲስ አንድ ህይወት፣ አዲስ ስም ፈልግ ፣ በልጅነትህ እናትህ ሁል ግዜ ፋንቱ ስለምትልህና ፣ ይህንን ስምህን ማንም ስለማያውቀው በግል ከኔ ጋር ለመገናኛነት ተጠቀምበት ። ግን ይህ የሚሆነው ግን ይህ በላያችንና በአገራችን ላይ ያንዣበበው መከራ ሲያልፍ ነው ። በል እንግዲህ ከአሁን በሁዋላ ስለማንገናኝ እግዚሐብሄር ከአንተ ጋር ይሁን። ገንዘብ እዛ እሽማግሌው ዘመድ ጋር ስላስቀመጥን ውሰድ ።እናትህን ለማግኘት እንዳትሞክር አሁን ተነስተህ ሂድ „ አለኝ ።

እኔም ለመጨረሻ አንተን ለማየት ቀረብ አልኩኝ ።እስቲ ልጠይቅህ አንተን ለመሆኑ የዛን ቀን እኔን አይተኸኛል ።ለኔ እንደገባኝ ያንን ሁሉ ስቃይ ችለህ አንድ መልክት ለኔ ለመንገር ያሰብክ መሆኑን ነው ። እኔ እንደገባኝ ምንም ሚስጥር አለወጣም በርታ የሚል ምልክት ነው ። መልሱኝ ስትል ወዲያ ነው ያወቅሁት መልክትህ እንዳለቀ።

ወጣሁ በረርኩ፣ በረርኩ፣በረርኩ፣በረርኩ፣ ሞቻለሁ እኔ የለሁም ። ቅዳሜ ለት ቤተሰቦቼ ይረዳሉ። ይለቀስ ይሆናል ወይ ይከለከላል። ለማንኛውም ግን እኔ ማን ነኝ እንግዲህ ። ውስጤን ልቀይር አልችል ይሆናል ግን ውጬን መቀየር አለበኝ ።ስሜስ ማን ይባላል ።እናቴ ገና ጥያት ሳልሄድ ኖፈቀችን ፣ አባቴ ኖፈቀኝ ፣ ሰፈሩ ኖፈቀኝ ፣ ጓደኞቼ ኖፈቁኝ፣ የወደፊቱን ሳስበው ጨለመብኝ ። ግን ደግሞ በቀይ ሽብር የተጎዳም ቢሆን ድርጅቴ አለልኝ ። ሁኔታውን ቀድመው ተዘጋጅውበታል ። ስደት የተደበቀ ኑሮ ተጀመረ ። የድጎማ አስተማሪ ሆንኩ።

እስቲ ለዛሬው እዚህ ላቁም

ስለኛ የሚያስብ በሰላም ይክረም !!!

- የእናንተ ነገር ጉድ ነው። ታውቃለህ  ይህንን ሁሉ እኔ እንደማላወቅ በተለይ የከርቼለውን ልጄ።
- ለኔም አዲስ ነው እናቴ ።

# ተፈፀመ።

ክቡራንና ክቡራን አንባቢያን ከዚህ በላይ ያለውን ታሪክ ለመፃፍ የአነሳሳኝ በአጋጣሚ እንደገና የተገናኘኋቸው የጓደኛ እናትና እረፍት ሁልጊዜ የሚነሳኝ ከአጠገቤ የተለዥኝ ጓዶቼ ትዝታ ሲሆን ወደፊት ሁለተኛውን ክፍል ጊዜ ሲኖረኝ ለማቅረብ እሞክራለሁ። በዚሁም ለደብተራውና ለአሲንባ ድህረ ገፅ አዘጋጆች ከፍ ያለ ምስጋናዬን እያቀረብኩ በፍኖተ ተጀምሮ የተቋረጠው ትረካም ወደ ፊት ጊዜ ሲገኝ እንደሚቀጥል ተሰፋ አለኝ። ብዙዎቻችን ብዙ ታሪክ በሚስጥር  ይዘን ሳንፀፈው ልናልፍ ስለምንችል በትንሹም ቢሆን ቢፃፍ ጥሩ ነው ብዬ አምናለሁ።

ታሪኩ ያለፈ ነው የሚሉ ወገኖች እንዳሉ አምናለሁ። ይህ ደግሞ የየግል አስተሳሰብ ነው። ለግማሾቻችን ገና ጥሬ ታሪክ ሲሆን ለሌሎቹ ደግሞ ያለፈ ነው። ግን ተፀፎ ቢቀመጥ የሚጎዳ ስላልሆነ ብዙዎቻችሁ እንድትሞክሩት አሳስባለሁ ።

በተረፈ ወቀሳም ይሆን ድጋፍ በአድራሻዬ ቢላክልኝ ለወደፊት ስለሚረዳኝ beljigali@beljigali.com በሚለው አድራሻ ቢላክልኝን ይደርሰኛል።

በግልም ይሁን በደብዳቤ እስካሁን የደገፋችሁኝን በዚሁ ምስጋኛዬን አቀርባለሁ።

በልጅግ አሊ።